# የመጽሐፍ ትችት

*መሐሪ ረዳኢ፣ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች፣ ቅጽ ሁለት፣ አዲስ አበባ፣ ኤፊሽንት ፕሪንቲንግ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም 194 ገጽ ብር 30*

ፊሊጶስ አይናለም በለጠ[•]

ይህ አጭር ጽሑፍ ረዳት ፕሮፌሰር መሐሪ ረዳኢ በጻፉት "የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች" ቅጽ ሁለት መጽሐፍ /አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም/ ላይ የቀረበን ትችት የያዘ ነው:: መጽሐፉ በተመሳሳይ ርዕስ የተጻፈው የቅጽ አንድ ቀጣይ ሲሆን በዋናነት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ/አዋጅ ቁጥር 213/92 ለመገንዘብ እንዲረዳ የተዘጋጀና አብዛኛውን የቤተሰብ ሕጉን ክፍል/አንቀጽ 123 እስከ 323/ ያካተተ ነው:: የመጽሐፉ አራቱም ምዕራፎች የህፃናትን ጉዳይ መሠረት ያደረጉ ናቸው::

በመጀመሪያው ምዕራፍ ህፃናት ከአባታቸው መወለዳቸውን ማረጋገጥ የሚቻለው በሕግ ግምት፣ አባት ነው የተባለው ሰው ልጅነቱን በመቀበሉ፣ እና በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነትን እንዲታወቅ በማድረግ መሆኑን ሰፊ ገለፃ ያደረጉበት ሲሆን ከእነዚህ ሦስት መንገዶች ውጭ ልጅነትን ስለማስረዳት በሚለው የሕጉ አተገባበር ምክንያት መወለድ የሚረጋገጥበት አራተኛ መንገድ እንደሌለ አስምረውበታል:: ፀሐፊው የአባትና የልጅን መብት ባጣጣመ ሁኔታ የመካድ ክስ ስለሚቀርብበት ሁኔታ በማንና መቼ ሊቀርብ እንደሚችል ልጅነትን ለመቀበል የአባትን፣ የልጁን እናትና የልጁንም ሚና በተመለከተ እንዲሁም የአባትነት ግጭት የሚፈታበትንና የልጅነት ማስረጃዎችንም በተመለከተ ጠበቅ ባለ ሁኔታ መታየት ያለበት ስለመሆኑ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተውበታል:: ልጅነትን ለመካድ በቀጥታ ስለሚቀርብ ክስ በሕጉ አንቀጽ 168 ላይ መሠረት በማድረግ /ገጽ 18/ የሰጡት ማብራሪያ በፍርድ ቤቶች ልጅነትን የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ሳይፈቅድ በማናቸውም ሁኔታ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን የተለመደ አቋም እንዲፈተሽና እንዲታረም ግንዛቤን የሚፈጥርና በእጅጉ የሚረዳ ነው::

በሁለተኛው ምዕራፍ የጉዲፈቻን ትርጉም ታሪካዊ አመጣጥ ስለጉቻ ስምምነትና ፎርም፣ የጉዲፍቻ ተደራጊውን ልጅ መብቶችን እንዲሁም ስለመንግሥትና የእጓለማውታን ድርጅቶች በጉዲፈቻ ስምምነት ያላቸውን ሚና በተመለከተ የቤተሰብ ሕጉን ከዓለም አቀፍ የሕፃናት ኮንቬንሽንና ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች ጋራ በማነፃፀር አብራርተዋል:: ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻው ገጽ ላይ የቤተሰብ ሕጉን

ከህፃናት መብት ኮንቬንሽን መጽደቅ በኋላ የወጣ መሆኑን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችና አስፈፃሚ አካላት አሠራር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው ከኮንቬንሽኑ ይልቅ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ነው ብለን እናምናለን በማለት የደመደሙበት ሃሣብ በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9/4/ እና 13/2/ ለዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከተሰጣቸው ቦታ እና ትኩረት ጋር የሚስማማ አይመስለኝም:: በቅርቡ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ/ሰ/መ/ቁ 23632 ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ/ም በፀዳለ ደምሴ እና ክፍሌ ደምሴ መካከል ከቤተሰብ ሕጉ ይልቅ ለዓለም አቀፍ ስምምነት የበላይነት በመስጠት ከተረጐመው ጋርም የሚስማማ አቋም አይደለም:: ዋናው ነገር መወሰድ ያለበት ለህፃናቱ ዓበይት ደህንነትና ጥቅም ቅድሚያ መስጠቱ ላይ ነው::

በመጽሐፉ ምዕራፍ ሦስት ለህፃናት ማደጊያ፣ ለትምህርት፣ ለጤናቸው፣ ለመጠለያቸው ለደህንነታቸውና ጥቅማቸው መጠበቂያ የሚሆን ቀለብ የማግኘት መብታቸውንና

---

[•] በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ እና በቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ህግ ፋክልቲ የትርፍ ጊዜ መምህር

የመስጠቱ ግዴታ የእነማን መሆኑንና ስለግዴታው መጠን፣ ግዴታውም ቀሪ የሚሆንበትን ሁኔታ በዝርዝር አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻው የመጽሐፉ ምዕራፍ አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን በሞግዚት ጥበቃ የማድረጉን አስፈላጊነት፣ አሳዳሪና ሞግዚት ስለሚሾምበት ሁኔታ ስለስራው ግዴታና ኃላፊነት/ተጠያቂነት እንዲሁም ሥልጣኑ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ በዝርዝር ማብራሪያ አድርገውበታል፡፡ይህ የመጽሐፍ ክፍል በፍርድ ቤት አከራካሪ ስለሆኑ አንዳንድ ጉዳዮች ለምሳሌ ሞግዚቱ የህፃኑን የማይንቀሳቀስ ሃብት በፍርድ ቤት ፈቃድ ወይም ያለፈቃድ መሸጥ ይችላል? አይችልም? ስለሚለው ጭብጥ የፍርድ ቤቶችን ክርክሮችና ውሣኔዎችን ዋቢ ያደረገ ማብራሪያ ቢጨመርበት የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረው ነበር፡፡ በጥቅሉ በዚህ ክፍል የቀረበው ትንተና ከተግባራዊ ጠቀሜታውና የሕጉ ዝርዝሮች አንፃር ሲፈተሽ መጠኑ አነስ ያለ ነው፡፡

ፀሐፊው በመጽሐፉ አራቱም ምዕራፎች አጠቃላይ የመነሻ ሃሳቦችን በማካተት የሕግ ባለሙያ ለሆነም ለአልሆነም በሚገባ ቋንቋ በጽሑፉ ከሚነሱት ጭብጦች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የዘመኑን ሣይንስ ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ባገናዘበ ሁኔታ ማህበራዊ ፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን /እንድምታዎችን/ እንዲሁም የቀደመውን ህግ እና በአንዳንድ የጽሑፉ ክፍሎች ደግሞ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ በመጥቀስ ያቀረቡት ንፅፅራዊ ገለፃ በእጅጉ ማራኪና በመጽሐፉ መግቢያ ያለሙትን ግብ ያስገኘላቸው ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ፀሐፊው የተሻሻለው  ሕግ የቀድሞው ሕግ ያልሸፈናቸውን ሁኔታዎች መሸፈኑን እና ለህፃናት መብት የተሻለ ጥበቃ ማድረጉን በዝርዝር አሳይተዋል፡፡ ፀሐፊው ስለልጅነት ማስረጃ /ገጽ 65-81/ የሰጡት ማብራሪያ በጭብጡ ዙሪያ በፍርድ ቤቶች በሚታዩ ክርክሮች ውሣኔ አሰጣጥ የሚታየውን የላላ/የለቀቀ/ የሕግ አተረጓጎም ልማድ ለማስቀረት /ቀዳዳ ለመድፈን/ የሚያስችል ነው፡፡

መጽሐፉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በፌዴራሉ ሕገ  መንግሥት አንቀጽ 36 እና በዓለም አቀፍ የሕፃናት ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 የተደነገገውን የሕፃናት መሠረታዊ መብቶች፣ ደህንነትና ጥቅም ቅድሚያ መስጠትን ትኩረት የሰጠና ይህንንም በመርህነት በመቀበል ዝርዝር ገለፃዎችን ያደረገና ለሕግ ተማሪዎች ፣ ለፍርድ ቤቶች ፣ ለሕግ አስፈፃሚም ሆነ በህፃናት መብት ዙሪያ ለሚሠሩ/ለሚንቀሳቀሱ አካላት ሁሉ ተግባራዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ የሆነ እንደ መሠረት ድንጋይ የሚያገለግል ተጨማሪ ምርምር ለሚያደርጉም መነሻ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ፀሐፊው ከላይ የተገለፀውን ለህፃናት መብት ቅድሚያ መስጠት እንደ መርሕ ተከትለው እያለ ግን በመጽሐፉ ገጽ 54 በፍ/ቤት ውሣኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ በሚለው ዋና ክፍል ሥር ገለፃቸውን ሲያጠቃልሉ በቤተሰብ ሕጉ ያልተካተተውን ከውል ውጭ ኃላፊነትን ሕግ የይርጋ ድንጋጌ በመጥቀስ ለቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 143 አፈፃፀም ልጅነትን ለማስወሰን የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ መገልገል እንደሚቻል ያሳሰቡት በሀገራችን ካለው የማህበረሰቡ ልጅነትን ለማስወሰን ክስ የማቅረብ ባህል /እውነታ/ የዳበረና የተለመደ ካለመሆኑም ባሻገር ለህፃኑ ዓበይት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ ከመስጠት አንፃር የሚያስማማ አይደለም፡፡ ከአጠቃላይ ከፅሁፋቸው አላማና ከአቋማቸው ጋርም አብሮ አይሄድም፡፡ እንደእኔ ሃሳብ ግን ቢያንስ ህፃኑ 18 ዓመት እስከሚሞላው ድረስ የልጅነት ይታወቅልኝ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ  ያለ ይርጋ ጥያ□ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ የቤተሰብ ሕጉም ይርጋውን በዝምታ ማለፉ አግባብነት አለው የሚል አቋም አለኝ፡፡  በተጨማሪም በመጽሐፉ ጥቂት በማይባሉ ክፍሎች( ለምሳሌ. በገጽ 11፣15 ፣ 20፣ 38 እና66) ይመስለኛል፣  ሊባል ይችል ይሆናል፣  ይገመታል . . .  በሚል የተጠቀሙት ግምታዊ አገላለጾች የጽሑፉን እርግጠኝነትና ክብደት የሚቀንስ ያስመስልባቸዋልና ቃላቱን ወይም ሀረጎቹን ባይጠቀሙ ይመረጥ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ግን የመጽሐፉ ይዘትና አፃፃፍ ዘዴ፣ በመጽሐፉ የተካተቱትን ጭብጦች ከመረዳት አልፎ ለሌሎች ተመራማሪዎችም እንደ ምሳሌ የሚወሰድ በመጽሐፉ ርእስ ከተመለከተው "አንዳንድ ነጥቦች" አልፎ ብዙ ነጥቦችን ያካተተና የሚያስገነዝብ የፀሐፊውን ግብም ያሟላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡